EARLY CHILDHOOD EDUCATOR PAY EQUITY FUND

# የበጀት አመት 2024 (FY24)
# የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ መርጦ የመግባት ሂደት
*የድጎማ አቅራቢዎች መመሪያዎች*

በFY24፣ OSSE በልጅ እድገት ተቋም (CDF) የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር አማካኝነት ለቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች ማካካሻ ለመጨመር የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፎች ክፍያን ለልጅ እድገት ተቋማት ያሰራጫል። የCDF የደመወዝ ክፍያ ቀመር ሽልማትን ለመቀበል፣ ተቋሙ በOSSE ፈቃድ ያለው እና ብቁ የሆኑትን የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች በስራ ደረጃ እና በዲግሪ፣ የFY24 ዝቅተኛ ደመወዞች የሚያሟሉ ወይም የሚበልጡ ደመወዞችን ለመክፈል መስማማት አለበት። ለመሳተፍ የሚፈልጉ የልጅ እድገት ተቋማት ወደ ፕሮግራሙ መርጠው መግባባት አለባቸው። መርጠው ለመግባት፣ በልጅ እንክብካቤ ድጎማ ፕሮግራም ("ድጎማ አቅራቢዎች") ውስጥ የሚሳተፉ የልጅ እድገት ተቋማት የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው፡-

**ደረጃ 1፥** ተቋሙ በFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ለመሳተፍ እንደሚፈልግ የሚያመለክተውን የFY24 የድጎማ ስምምነት እድሳት ማመልከቻ (SARA) ይሙሉ እና ያስገቡ።

**ደረጃ 2፥** የFY24 ቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ አቅራቢ ስምምነት ተጨማሪ ጽሁፍን ማጠናቀቅ።

ይህ መመሪያ ለድጎማ አቅራቢዎች እንደ የFY24 SARA መተግበሪያ አካል የFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ መርጠው እንዲገቡ መመሪያዎችን ይሰጣል። ድጎማ አቅራቢዎች ሙሉውን የSARA ማመልከቻ ማሟላትን በተመለከተ መረጃ ለማግኘት የFY24 SARA ማመልከቻን ለመሙላት የተቀበሉትን መመሪያ ማጣቀሻ ማድረግ አለባቸው።

ተቋሙ የ SARA ማመልከቻን በ DELLT ውስጥ ሞልቶ ካስገባ በኋላ፣ OSSE ሁሉንም የቀረቡ ሰነዶችን ይገመግማል። ከግምገማ በኋላ፣ OSSE እንደ FY24 SARA አካል የ FY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ አቅራቢ ስምምነትን ያጋራል።

የድጎማ አቅራቢዎች የ **SARA ማመልከቻ** በ DELLT ለመሙላት እና ለማስገባት ቀነ ገደቡ **አርብ ኦገስት 18፣ 2023 5 p.m.** ላይ **ነው።** በ SARA ማመልከቻው ውስጥ በ FY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ላይ ፍላጎት እንዳላቸው ያላሳዩ ድጎማ አቅራቢዎች፣ በ FY24 የሩብ አመት አንድ የCDF የደመወዝ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማት ለመቀበል ብቁ ለመሆን ለትምህርት አገልግሎቶች ክትትል (ESM) በፕሮግራሙ

ውስጥ ለመሳተፍ ያላቸውን ፍላጎት ለማሳወቅ እስከ **አርብ፣ ሴፕቴምበር 15፣ 2023 5 p.m.** ድረስ ጊዜ አላቸው። ከዚያም ESM መርጦ የመግባት ሂደቱን ይጀምራል።

ለFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ቁልፍ ማስረከቢያ ቀነ ገደቦች በሚቀጥለው ገጽ ላይ ይገኛሉ። አንድ ጊዜ አቅራቢው መርጦ የመግባት ሂደቱን ካጠናቀቀ እና በ FY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ስምምነት ተጨማሪ ጽሁፍ ከተፈጸመ በኋላ፣ የፕሮግራሙን መስፈርቶች ማሟላታቸውን ከቀጠሉ የቀሩትን የFY24 የሩብ አመት ክፍያዎችን ወዲያውኑ ያገኛሉ።


| **FY24 መርጦ የመግባት እና የስምምነት ማስረከቢያ ቀነ ገደቦች**<br>**ሁሉም ቀነ ገደቦች 5 p.m. ላይ ናቸው ET* | | | |
|---|---|---|---|
| **ሩብ ዓመት** | **የድጎማ አቅራቢ መርጦ የመግባት ቀነ ገደቦች** | **የአቅራቢ ስምምነት ቀነ ገደብ** | **የክፍያ ስርጭት** |
| ሩብ አመት አንድ | ሴፕቴምበር 15፣ 2023 | ሴፕቴምበር 30፣ 2023 | ዲሴምበር 2023 |
| ሩብ አመት ሁለት | ዲሴምበር 15፣ 2023 | ዲሴምበር 31፣ 2023 | ማርች 2024 |
| ሩብ አመት ሶስት | ማርች 15፣ 2024 | ማርች 31፣ 2024 | ጁን 2024 |
| ሩብ አመት አራት | ጁን 15፣ 2024 | ጁን 30፣ 2024 | ሴፕቴምበር 2024 |

በFY24 SARA ማመልከቻቸው ለመሳተፍ ፍላጎት እንዳላቸው ያላያሳዩ ድጎማ አቅራቢዎች ወደ FY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ መርጠው መግባት እንደሚፈለጉ ለESM ቅጻሜ ሰኔ 15፣ 2024 እስከ 5 p.m. ድረስ ማሳወቅ ይችላሉ (ለሩብ አመት አራት መርጦ የመግባት ቀነ ገደብ)። የESM ማስታወቂያ ከደረሰው በኋላ፣ መርጦ የመግባት ሂደቱን ይጀምራሉ። ተቋማት ለእያንዳንዱ ሩብ አመት መርጦ የመግባት እና የስምምነት ቀነ ገደቦችን ማስታወስ አለባቸው። ለዚያ ሩብ አመት የCDF ደመወዝ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማት ለማግኘት የልጅ እድገት ተቋም ከላይ የታዘዘውን የሩብ አመት ማመልከቻ እና የስምምነት ቀነ ገደብ ማሟላት አለበት።


## በSARA ማመልከቻ ወደ FY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ መርጦ የመግባት ደረጃዎች

**ደረጃ 1፡ ወደ DELLT ይግቡ።**


**ደረጃ 2፡ የ FY24 SARA ማመልከቻ ለማግኘት "የድጎማ እድሳት እና ክፍያ ፍትሃዊነት ስምምነቶች" የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።**



**ደረጃ 3፥ “የድጎማ እድሳትን ጀምር እና የፍትሃዊ ክፍያ ስምምነቶችን ጀምር” የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።**





**ደረጃ 4፥ የእርሳስ አዶውን ጠቅ ያድርጉ።**




**ደረጃ 5፥ በተቋም መረጃ ክፍል ውስጥ ያለውን የእርሳስ አዶ ጠቅ ያድርጉ።**

በSARA መተግበሪያ ውስጥ ወደ ቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ እና የተቋም መረጃ ክፍል ይሸብልሉ። በቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ክፍል ውስጥ ምንም እርምጃ አያስፈልግም። በልጅ እንክብካቤ ድጎማ ፕሮግራም ውስጥ የሚሳተፉ ብዙ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ከሆነ፣ እያዳንዱ ተቋም በተቋም መረጃ ክፍል ውስጥ ይዘረዘራል። በፕሮግራሙ ውስጥ እንዲሳተፍ ከሚፈልጉት ተቋም ቀጥሎ ያለውን የእርሳስ አዶን ጠቅ ያድርጉ።



**ደረጃ 6፡ ተቋሙ በ FY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ላይ መሳተፍ እንደሚፈልግ ያመልክቱ።**

“በቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ውስጥ ለመሳተፍ ፍላጎት አለዎት” ከሚለው ቀጥሎ ባለው ሳጥን ላይ ምልክት ያድርጉ። እንዲሁም ለSARA ማመልከቻ እንደ አስፈላጊነቱ የድጎማ የልጅ እንክብካቤ አቅራቢ አገልግሎቶች ቅጽን እና የሰራተኛ ንድፍን መስቀል ያስታውሱ። ግቤቱን ለማስቀመጥ “አስቀምጥ እና ዝጋ” የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።





**ደረጃ 7፡ በFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ውስጥ ለመሳተፍ በሚፈልጉ የተቋም መረጃ ክፍል ውስጥ ለተዘረዘረው እያንዳንዱ ተቋም ደረጃ 5 እና 6ን ይድገሙ።**

## ጥያቄዎች?

የFY24 SARA ማመልከቻን ለመሙላት ጥያቄዎች ያላቸው ወይም ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ድጎማ አቅራቢዎች በDELLT ውስጥ የመልዕክት መላላኪያውን እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ። የመልዕክት መላላኪያ ባህሪን ለመጠቀም መመሪያዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል። አቅራቢዎች ለድጋፍ የእነርሱን ESM በቀጥታ ማግኘት ይችላሉ።


**ደረጃ 1፥ ወደ የአቅራቢው መግለጫ ይሂዱ።**

**ደረጃ 2. "መልዕክቶች" የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።**



**ደረጃ 3፥ ጥያቄ ያስገቡ።**

መልዕክትዎን በዋናው ክፍል ውስጥ ይተይቡ። መልዕክቱን ለመላክ “አስቀምጥ እና ዝጋ” የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።



## ተጨማሪ መረጃ

በ FY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎን osse.dc.gov/fy24ecepayequityን ይጎብኙ። ፈልገው ሊያገኟቸው የሚችሏቸው ግብዐቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

- FY24 CDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር
- FY24 ዝቅተኛ የደመወዝ እና የደመወዝ መስፈርቶች
- ለልጅ እድገት ተቋም መሪዎች FAQ